ጀናዛን ፈጠን ብላችሁ ቅበሩ። ጀናዛው መልካም ከሆነ ወደ መልካም ነገር ማስቀደም ነው። ከዛ ውጪ ከሆነ ደግሞ መጥፎ ነገር ነው ከትከሻችሁ ማላቀቅ ነው።

ከአቡ ሁረይራ ረዺየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ
ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- እንዲህ ብለዋል: "ጀናዛን ፈጠን ብላችሁ ቅበሩ። ጀናዛው መልካም ከሆነ ወደ መልካም ነገር ማስቀደም ነው። ከዛ ውጪ ከሆነ ደግሞ መጥፎ ነገር ነው ከትከሻችሁ ማላቀቅ ነው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ጀናዛን ለቀብር ማሰናዳት፣ ጀናዛው ላይ መስገድና መቅበር በፍጥነት እንዲከናወን አዘዙ። ጀናዛው መልካም ከሆነ ወደ መልካሙ የቀብር ፀጋ እያስቀደማችሁት ነው፤ ከዛ ውጪ ከሆነ ደግሞ መጥፎን ነገር ከትከሻችሁ እየተላቀቃችሁ ነው አሉ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3109